# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከኤፕሪል 1-10/2022 የነበረው የአየር

## ሁኔታ ግምገማ እና

## ከኤፕሪል 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

## ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኤፕሪል 2022
አዲስ አበባ

**ርዕስ** **ገፅ**


እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ....... 3

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10 /2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....... 4

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10 /2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ....... 5

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10 /2022 ድረስ የነበረው የዝና ብመጠን ....... 6

ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ....... 6

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....... 7

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....... 7

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....... 8

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....... 8

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ ....... 9

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....... 10

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....... 10


## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

በኤፕሪል የመጀመሪያው አስር ቀናት ለበልግ ዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በደቡብ፣ በደቡብ በምዕራብ እና በደቡብ ከፍተኛ ስፍራዎች ባሉት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ካለፈው ጊዜ አንጻራዊ በሆነ መልኩ መሻሻል በማሳየታቸው ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እንዲሁም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ በተለያዩ ቀናት ተመዝግቧል፡፡ በመሆኑም ከባድ ዝናብ ከመዘገቡ ስፍራዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በአቦቦ 40.6፣ በድሬዳዋ 43.6፣ በጋምቤላ 31.6 እንዲሁም በጊኒር 50.5 በሚ.ሜ. ይጠቀሳሉ።


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ከአማራ ሰሜን ጎንደርና በአዊ ዞኖች ጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ፤ በአሶሳ፤ በጋምቤላ፤ በአብዛኛው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ ከኦሮሚያ በኢሉአባቦር፣ በጂማ፣ በምዕራብና ቄሌም ወለጋ፣ በሆሮጉዱሩ ወለጋ እና በአርሲና ባሌ ክልል ዞኖች፣ እንዲሁም በድሬዳዋ ከ5-92 ሚሜ የሚደርስ ከ2-9 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነጻፀር በአሶሳ፣ በጋምቤላና በምዕራብ አማራ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ የተቀሩት አብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በአመዛኙ ከመደኛው በታች የሆነ የዝናብ መጠን የነበራቸው ሲሆን፤ ደረቅና ፀሐያማ የአየር ሁኔታ የጎላ ተፅዕኖ ነበረው (ካርታ 3) ፡፡


ካርታ 1   እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10 /2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2 ኢ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10 /2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



**ካርታ 3   ኢ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10 /2022 ድረስ የነበረው የዝና ብመጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር**





ከመደበኛ በታች          መደበኛ          ከመደበኛ በላይ

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት የኤፕሪል 2022 የመጀመሪያ አሥር ቀናት ወደ ሀገራችን እየገባ የነበረዉ ዕርጥበት አዘል አየር በአብዛኛዎቹ የበልግ አብቃይ እና ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ የተሻለ ገጽታ ነበረው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም ባለፉት አስር ቀናት አብዛኛዎቹ የበልግ ተጠቃሚ ላይ በተለይም በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ ባሉት የሀገሪቱ አካባቢዎች ካለፈው ጊዜ አንጻራዊ በሆነ መሻሻል በማሳየታቸው ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ በተለያዩ ቀናት ተመዝግቧል፡፡ በመሆኑም የተገኘው እርጥበት የተሻለ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የበልግ እርሻ ስራ እንቅስቃሴ እያካሄዱ ላሉ አካባቢዎች ለሰብሉ የውሃ ፍላጎት መሟላት፣ ለረጅም ጊዜ ሰብሎች የማሳ ዝግጅትና የዘር ጊዜ እርሻ እንቅስቃሴ፣ ለቋሚ ተክሎች የዉሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም ከላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች ለሚገኙ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለመጠጥ ውሀና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት ጠቀሜታ ነበረው። ከዚህ በተፀራሪ በተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች የነበረው አነስተኛ ዝናብ ከፀሐያማና ሞቃታማ የአየር ሁኔታ ጋር ተዳምሮ በወቅቱ አጠቃላይ የግብርና ሥራ እንቅስቃሴ እና የሰብሎች ዉሃ ፍላጎት ማሟላት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደአሳደረ ያመላክታል (ካርታ 4) ፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 1-10 ኤፕሪል 2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ የነበራቸው ተፋሰሶች በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ መካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው ገናሌ ዳዋ፣ ዋቢሸበሌ፣ በጥቂት የታችኛው አዋሽ እንዲሁም በጥቂት በታችኛው የአባይ ኪስ ቦታዎች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ ከፍተኛ እርጥበት የነበራቸው ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ አመዝኖባቸው ነበር (ካርታ 5) ፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




# እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ


በመደበኛ ሁኔታ በኤፕሪል ሁለተኛው አሥር ቀናት የዝናቡ መጠንና ሥርጭት ከቀዳሚ አሥር ቀናት በተሻለ መልኩ በአብዛኛው የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን የሚያዳርስበት ጊዜ ነው፡፡ በተለይም የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች በወቅቱ ውስጥ ከፍተኛ የዝናብ መጠን ያገኛሉ፡፡

በሚቀጥሉት የኤፕሪል ሁለተኛው አሥር ቀናት ወደ ሀገራችን እርጥበት አዘል አየር ለመግባት አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ከቀደመው አሥር ቀናት አንጻር ሲታይ በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ አጋማሽ፣ በመካከለኛዉና በምስራቅ የአገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ሁኔታ እንደሚኖር ከመጠበቁ ጋር በተያያዘ ዝናቡ በመጠንም ሆነ በሥርጭት በአንጻሩ የተሻለ ጥንካሬ ሊኖራቸዉ እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ቄልምና ምዕራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ የምዕራብና የደበቡ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፣ የምዕራብና የምሥራቅ ሐረርጌ፣ አርሲና ቦሌ፣ አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋና ሀረሪ፤ ከሶማሌ ክልል የፋፈን እና የሊበን  ዞኖች፤ ከጋምቤላ ክልል የአኞክና የመዠንግ ዞኖች፤ ሁሉም የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዞኖች፤ የሲዳማ ዞኖች እና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል  የሰሜን ወሎ ዞኖች፣ ደቡብ ጎንደር፣ ምሥራቅ እና ምእራብ ጎጃም፣ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ሊኖራቸዉ እንደሚችል የሚጠበቅ ሲሆን፤ በተጨማሪም የባህርዳር ዙሪያ፣ ጥቂት የሰሜን ጎንድር ዞኖች፤ ከሶማሌ ክልል ሲቲ፣ ኖጎበ፣ አፍዴር፣ የሸበል እና የቆራሂ ዞኖች፤ቦረናና ጉጂ፣ የደቡብ ዎሎ፤ ከትግራይ ክልል የምዕራብና የሰሜን ዞኖች፤ የአፋር ክልል ዞን 5 በአንዳንድ ሥፍራዎቻቸው ላይ ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች አመዛኙ ደረቅና ሞቃታማ  ሆነው ይሰነብታሉ።




እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 11-20, 2022 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ.




እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 11-20, 2022 የሚኖረዉ የቀኑ ከፍተኛ የአየር ሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

እ.ኤ አ በመደበኛ ሁኔታ የኤፕሪል ወር ከመጀመሪያው አሥር ቀናት ጀምሮ የእርጥበት ሁኔታው በበልግ አብቃይ አካባቢዎች የሚሻሻልበትና ለበልግ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት የሚቻልበት ወቅት ሲሆን፤ በተጨማሪም የሚገኘው እርጥበት ለአርብቶ አደሩ አካባቢ ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚሰጥበት ወቅት ነው፡፡

ከላይ በተገለፀው ትንበያ መሰረት በሚቀጥለው የኤፕሪል ሁለተኛው አስር ቀናት ከቀደመው አሥር ቀናት አንጻር ሲታይ የእርጥበት ሁኔታው እንደሚጨምርና ካለፈው አስር ቀን የተሻለ እንደሚሆን የሚጠበቅ ሲሆን፤ በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ ኢጋማሽ፣ በመካከለኛዉና በምስራቅ የአገሪቱ ክፍሎች ላይ በይበልጥ የተጠናከር እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ በትንበያው ላይ ለተጠቀሱት የበልግ አብቃይ እና ተጠቃሚ አካባቢዎች ለሚያከናውኑት የግብርና እንቅስቃሴ አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር የሚጠበቅ ሲሆን፤ በተለይም ባሳለፍናቸው ተከታታይ ቀናቶች በደቡብ ኢጋማሽ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉና በምስራቅ የአገሪቱ ክፍሎች ላይ በተከታታይ ከነበረው ደረቅ ሰሞናት ጋር ተያይዞ የተፈጠረውን የእርጥበት እጥረት እንደሚያረግብ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም ቀደም ብለው ለተዘሩና በቡቃያ ደረጃ ላሉም ሆነ ለቋሚ ሰብሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት በተጨማሪም የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት ምቹ ሁኔታ እንደሚኖር የሚጠበቅ በመሆኑ፤ አርሶ አደሮች ተገቢ የሆኑ ግብአትን በማካተት የእርሻውን ሥራውን ለማካሄድ አስፈላጊ ዝግጅት ሊያደረጉ ይገባል፡፡ እንዲሁም የሚጠበቀው እርጥበት ለአርብቶ አደሮችና ለከፊል አረብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውኃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል እርጥበት አጠር የሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን ውኃ የተለያዩ የዉሃ ማቆያ ዘዴዎችን አጠናክሮ በመስራት በመካከል ለሚገጥሙ ደረቅ ሰሞናት አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ማድርግ ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የኤፕሪል ሁለተኛው አስር ቀናት አብዛኛዎቹ የበልግ ተጠቃሚ ተፋሰሶች ላይ ከባለፈው የተሻለ እርጥበት መጠን ሊኖራቸው እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በዚህ

መሰረት በአብዛኛው ስምጥ ሸለቆ፣ ኦሞጊቤ፣ አዋሽ፣ የላይኛዉና የመካከለኛ አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ ገናሌዳዋ እና ዋቢሸበሌ፣ የላይኛዉ ተከዜ እንዲሁም የላይኛዉ አፋር ደናክል ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ ከፍተኛ እርጥበት እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም ይህ ሁኔታ ለወራጅ ውሃ አዎንታዊ አስተዋፆ ይኖረዋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ሆኖም በበልግ ከፍተኛ ሙቀት ምክንያት በትነትና በተለያየ መልክ የሚባክነውን የዉሃ ሀብት የተለየዩ ዘዴዎችን በመጠቀም መታደግ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል ለቅፅበታዊ ጎረፍ እና ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ቦታዎችም መዘጋጀት ያሻል፡፡